## የምድብ ዓይነቶች እና የቅይይር ስሌቶች ፡ ሁለት

## የቃላት ጥያቄዎች

1. 1ኪ.ሜ$^2$ ከየትኛው ምድብ ጋር እኩል ነው ?

   ሀ) 1000 ሜ$^2$ ለ) 100000 ሳ.ሜ$^2$

   ሐ) 1000000 ሚ.ሜ$^2$ መ) ሀ እና ለ

2. የሳሚ አባት ቁመት 2ሜ ነው፡፡ ሳሚ ደግሞ ቁመቱ 1ሜትር ከ 35 ሳ.ሜ ነው ፡፡ 20 ሳ.ሜ በርጨማ ላይ ቢወጣ የአባቱ ቁመት ላይ መድረስ ይችላል ወይስ አይችልም?

   ይችላል አይችልም

   2.1. የሳሚ ቁመት ከአባቱ ቁመት ምን ያህል ሳ.ሜ ልዩነት አለው ?

   ሀ) 15 ሳ.ሜ ለ) 5 ሳ.ሜ ሐ) 10 ሳ.ሜ መ) 0 ሳ.ሜ

3. በከፍተኛ ዝላይ ውድድር ላይ እያንዳንዱ አትሌት 3 ሜ የሚሆን ርቀት መዝለል አለበት ፡፡ ሶፊያ በመጀመሪያ ዝላይ 3.19 ሜ ዘለለች ፡፡ ሃና ደግሞ ሶፊያ ከዘለለችው ርቀት 35 ሳ.ሜ ጭማሪ ዘላለች፡፡ ሃና የዘለለችው ርቀት ስንት ሳ.ሜ ይሆናል ?

   ሀ) 35.4 ሳ.ሜ ለ) 3.54 ሳ.ሜ

   ሐ) 354 ሳ.ሜ መ) 0.354 ሳ.ሜ

4. ናሆም ቁመት 125 ሳ.ሜ ሲሆን የጓደኛው የሄኖክ ደግሞ 138 ሳ.ሜ ነው ፡፡ ከ 1 ዓመት በኋላ ናሆም 40 ሳ.ሜ ቁመት ሲጨምር ሄኖክ ደግሞ 25 ሳ.ሜ ቁመት ጨምሯል ፡፡ በናሆም እና በሄኖክ መካከል ምን ያህል ልዩነት አለ ?

   ሀ) 20 ሳ.ሜ ለ) 2 ሳ.ሜ ሐ) 0.02 ሜ መ) ለ እና ሐ

LIVEWORKSHEETS




5. ቀነኒሳ በ 20 ደቂቃ ውስጥ 1.2 ኪ.ሜ መሮጥ ከቻለ፣ በ አንድ ደቂቃ ስንት ሜትር መሮጥ ይችላል ?

ሀ) 60 ሜ ለ) 600 ሜ

ሐ) 120 ሜ መ) 6 ሜ

6. አንድ የሸክላ ጡብ 12 ሚ.ሜ ውፍረት አለው ፡፡ 110 የሸክላ ጡቦች ተነባብረው ቢቀመጡ ምን ያህል ሜትር ቁመት ይሆናል?

ሀ) 60 ሜ ለ) 600 ሜ

ሐ) 120 ሜ መ) 6 ሜ

7. አንድ ኤሊ በ 27 ደቂቃ ውስጥ 567 ሚ.ሜ ትጓዛለች፡፡ በ አንድ ደቂቃ ውስጥ ምን ያህል ሳ.ሜ መጓዝ ትችላለች?

ሀ) 11 ሳ.ሜ ለ) .21 ሳ.ሜ

ሐ) 2.1 ሳ.ሜ መ) 21 ሳ.ሜ

8. የአንድ ላጲስ ውፍረት 10 ሚ.ሜ ቢሆን ፣ አንድ ባለሱቅ 230 ላጲሶችን ወደላይ ደርድሮ ለማስቀመጥ ምን ያህል ሴንቲ ሜትር ቁመት ቦታ ይወስድበታል ?

ሀ) 0.1 ሳ.ሜ ለ) 23 ሳ.ሜ

ሐ) 2.3 ሳ.ሜ መ) 0.23 ሳ.ሜ

9. አንድ የስጦታ እቃን ለማሸግ 20 ሳ.ሜ ሪቫን ይፈልጋል ፡፡ 6 ሜትር ሪቫን ምን ያህል የስጦታ እቃዎችን ማሸግ ይቻላል ?

ሀ) 45 ሳ.ሜ ለ) 35 ሳ.ሜ

ሐ) 30 ሳ.ሜ መ) 0.3 ሳ.ሜ

LIVEWORKSHEETS

10. 1.2 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና 6 ሜትር ወርድ ያለውን የሰፈራችንን መንገድ ርዝመቱ 24 ሳ.ሜ እና ወርዱ 15 ሳ.ሜ በሆነ ሸክላ ለማንጠፍ ስንት ሸክላዎች ያስፈልጉናል ?

ሀ) 20,000 ለ) 2,000

ሐ) 120,000 መ) 200,000

11. የአንድ የመመገቢያ ክፍልን ለማንጠፍ ርዝመቱ 12 ሳ.ሜ ወርዱ ደግሞ 10 ሳ.ሜ የሆነ 100 ሸክላዎች ቢያስፈልገን የክፍሉ ስፋት ምን ያህል ሜ$^2$ ነው ?

ሀ) 1200 ሜ$^2$ ለ) 120 ሜ$^2$

ሐ) 12000 ሜ$^2$ መ) 12 ሜ$^2$

LIVEWORKSHEETS